# ቤርያ

ቁጥር 38

በየወሩ እየታተመ በወረቀት፣ በኢሜይል፣ በፌስቡክ እና በቴሌግራም በነጻ የሚሰራጭ መጽሄት

እነዚህም [የቤርያ ሰዎች] በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና፦ ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው እለት እለት መጻህፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ



| | |
|---|---|
| አዘጋጅ - አበበ መንገሻ (ዶ/ር)<br>አድራሻ - ዱላ ከተማ<br>ስ.ቁ. – 0936669160 | ኢሜይል - abebe.meng@gmail.com<br>ፌስቡክ ገጽ - Berea teaching<br>ቴሌግራም https://t.me/bereamagazineethiopia |


## የበአላት አከባበር (ክፍል 1)

እኛ ኢትዮጵያውያን ከየትኛው ህዝብ የበለጠ በአል ማክበር እንወዳለን ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ እንደማስረጃ በአገራችን አንድ ክፍል ከወሩ ሰላሳ ቀናት መካከል አስራ ዘጠኙ ስራ የማይሰራባቸው አስገዳጅ በአላት እንደሆኑ አንድ የእርዳታ ድርጅት ሰራተኛ ያጫወተኝን መጥቀስ እችላለሁ፡፡ በዚያ ቦታ ይህ የስራ ቀናትን በበአል ምክንያት ማባከን ሌሎች ተፈጥሯዊ ችግሮች ተደማምረውበት ህዝቡን ለድህነት እንደዳረገው እና ሁልጊዜም የእርዳታ ድርጅቶችን እጅ እንዲጠባበቅ እንዳስገደደው ከዚህም የተነሳ ከየትኛውም የአገሪቱ ክፍል በበለጠ ብዙ የርዳታ ድርጅቶች በአካባቢው እንደሚገኙ ሰውየው ጨምሮ ነገሮኛል፡፡

እነዚህ ሰዎች አስራ ዘጠኙን ቀናት ለማበል የወሰኑት የሀይማኖት መጻህፍትን መሰረት በማድረግ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡ ነገር ግን የውሳኔያቸው ትክክል መሆን አለመሆን የሚመዘነው በዋናው የእግዚአብሄር መጽሀፍ አማካይነት ነው፡፡ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ መጽሀፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን የደነገጋቸውን በአላት፣ የበአላቱን መንፈሳዊ ትርጉም፣ በአዲስ ኪዳን መጻህፍት ውስጥ ስለበአል የተሰጡ ሀሳቦችን እና እኛ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ የሆኑ እና መንፈሳዊ ያልሆኑ በአላትን ስናከብር መከተል ያሉብንን መንገዶች እንመለከታለን፡፡

### በአል በብሉይ ኪዳን

በአል ማለት ከመደበኛ ድርጊቶች ታቅቦ ወይም ነጻ ሆኖ በልማድም ይሁን በሃይማኖታዊ ትዕዛዝ ወይም በዕቅድ የተመደቡ ስርአታዊ ክንዋኔዎችን ወይም የመዝናናት ስራዎችን በመስራት ወይም እረፍት በማድረግ የምናሳልፈው ቀን ማለት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ሰዎች ከማንኛውም ስራ ታቅበው የአምልኮ ስርአቶችን በማከናወን የሚያሳልፏቸው አንድ በየሳምንቱ፣ ስምንት በየአመቱ፣ አንድ በየሰባት አመቱ እና አንድ በየሀምሳ አመቱ የሚከበሩ በድምሩ አስራ አንድ በአላት ነበሩ፡፡ ከእነዚህ መካከል ዘጠኙ ማለትም ሰንበት፣ ፋሲካ፣ የዳስ በአል፣ የቂጣ በአል፣ መለከት የሚነፋበት ቀን፣ የማስተስረያ ቀን፣ የመከር በአል (በአለ ሀምሳ)፣ የሰንበት አመት እና ኢዮቤልዩ እግዚአብሄር በቀጥታ ያወጃቸው በአላት ናቸው፡፡ አንድ አይሁዳዊ በመለኮታዊው ትእዛዝ መሰረት በአማካይ በወር 5.8 ቀን ስራ እንዳይሰራ እና ሀሳቡን ሰብስቦ እግዚአብሄርን እንዲያመልክ ይጠበቅበታል፡፡ አይሁድ እነዚህን በአላት በማክበራቸው ምክንያት በኢኮኖሚም ይሁን በጸጥታ በኩል ምንም ችግር እንደማይገጥማቸው እንዲያውም የበለጠ እንደሚባረኩ ቃል ተገብቶላቸዋል (ዘሌ 25፡18-19)፤ እንደተገባላቸውም ቃል በተግባር በእውነተኛ ልብ እግዚአብሄርን ለማምለክ በቀደሷቸው በአላት ምክንያት የገጠማቸው ችግር አልነበረም፡፡ ሌሎቹ ሁለቱ ማለትም ፑሪም እና የመቅደስ መታደስ በአል ደግሞ በኋላ በህዝብ የተጨመሩ ወይም የተሰየሙ በአላት ናቸው፡፡

1. <u>ሰንበት</u>

ሰንበት የሚባለው እግዚአብሄር ራሱ አብሎ በምሳሌነት ያሳየው የሳምንት የመጨረሻው ቀን ሲሆን በዚህ በአል ማንኛውንም ስራ መስራት አይፈቀድም፤ ሰውም ሆነ እንስሳ ከየትኛውም ተግባር የማረፍ ግዴታ አለበት (ዘጸ 20፡8-11)፡፡ እንዲሁም የአምልኮ ጉባኤ ይከናወንበታል (ዘሌ 23፡3)፡፡ ለማንኛውም ሰው ስራ አለመስራቱ ምንም የሚያጎድልበት ገቢ ካለመኖሩም ባሻገር ለመስራት የሚነሳ ሁሉ በሞት ይቀጣል (ዘጸ 31፡14)፡፡ ብሉይ ኪዳን ጥላ እንደመሆኑ

መጠን ሰንበትም በትንቢታዊ ትርጉሙ በክርስቶስ የሚገኘውን የዘላለም እረፍት ወይም መንግስተ ሰማያትን ያመለክታል (እብ 4፡9)፡፡ ለግል ህይወታችን ስናዛምደው ደግሞ በጌታ ላይ ሁሉን ጥለን ከጭንቀት እና ከሀሳብ ነጻ መሆን እንዳለብን ያሳየናል፡፡

2. <u>ፋሲካ</u>

ፋሲካ በአመቱ የመጀመሪያው ወር በአስራ አራተኛው ቀን በግ አርዶ ስጋውን ከመራራ ቅጠልና እርሾ ካልገባበት ቂጣ ጋር በመብላት እንዲሁም ስራ ባለመስራት የሚከበር በአል ሲሆን ንጹህ የሆነ ሰው ሁሉ ይህን በአል ካላከበረ ይቀጣል (ዘጸ 12፡1-20፤ ዘሌ 23፡5-7፤ ዘሁ 9፡34)፡፡ በአሉ አይሁድ በግብጽ ከተያዙበት የሰው እና የሰይጣን ባርነት ነጻ ሆነው ሀገሩን ጥለው የመውጣታቸው መታሰቢያ ነው (NIV Study Bible, 1985:176-177፣ Shepherd's Staff, 1993:C104-105) ፡፡ ፈርኦን ብቻውን እንዳይደለ እና ሰይጣን በውስጡ ሆኖ እሱም በባርነት እንደያዛቸው የምናውቀው በዘውዱ ላይ ከፊት ለፊቱ የኮብራ ምልክት መኖሩን ስንመለከት ነው፡፡ ይህ ፋሲካን እስራኤል ከፈርኦን ባርነት ብቻ ሳይሆን ከሰይጣን አገዛዝም ነጻ የወጡበት ሁኔታ መታሰቢያ ያደርገዋል (Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡ በጥላነቱ ደግሞ የኢየሱስን መሰቀል ሲያመለክት በግል ህይወታችንም የእግዚአብሄር በግ በሆነው በክርስቶስ ሞት ምክንያት ከሃጢያት ባርነት፣ ከዘላለም ሞት፣ ከሞቱ ስራዎች መዳንና ወደአዲስ ህይወት፣ ወደአዲስ ቤተሰብ፣ ወደአዲስ ዘር እና ወደአዲስ ኪዳን መግባታችንን ያሳያል (2ቆሮ 10፡17፤ Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡

3. <u>የዳስ በዓል</u>

የዳስ በአል የአዝመራ ማከማቻ በዓል ነው፡፡ አይሁድ ከግብጽ ወደከነአን በሚጓዙበት ወቅት በምድረ በዳ በጊዜያዊ መጠለያ መኖራቸውን ለማስታወስ እህል ከተከማቸ በኋላ በሰባተኛው ወር ከአስራ አምስተኛው ቀን ጀምሮ ለሰባት ተከታታይ ቀናት በዳስ ውስጥ እየተቀመጡ አምላካቸውን ያመሰግኑ ነበር (ዘሌ 23፡39-43፤ NIV Study Bible, 1985:176-177)፡፡ በመጀመሪያው እና በስምንተኛው ቀናት ሁሉም ሰው ከስራ ሁሉ ታቅቦ በአምልኮ ጉባኤ ይሳተፋል (ዘሌ 23፡35-36፣ 39)፡፡ በተለይ ወንድ ሁሉ ወደቤተ መቅደሱ መጥቶ አምልኮውን መፈጸም ግዴታው ነው (ዘጸ 34፡18-23፤ ዘዳ 16፡16)፡፡ ለአዲስ ኪዳን ያለው ትንቢታዊ ትርጉም በመጨረሻው ቀን በክርስቶስ ዙፋን ፊት የህዝቡን መሰብሰብና የአካሉን ሙሉ መሆን ሲሆን ከግል ህይወታችን ጋር ስናዛምደው ደግሞ በክርስቶስ አማካይት ወደቅድስና ፍጹምነት መድረሳችንን ይጠቁመናል (Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡

4. <u>የቂጣ በዓል</u>

የቂጣ በአል በመጀመሪያው ወር ከፋሲካ ማግስት ጀምሮ ለአንድ ሳምንት የሚከናወን በአል ሲሆን በበአሉ የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ቀናት የአምልኮ ጉባኤ ይደረግበታል (ዘሌ 23፡6-8)፡፡ ተጨማሪ የአምልኮ ተግባራቱ ቂጣ መብላት እና መስዋዕት ማቅረብ ናቸው፡፡ ልክ እንደዳስ በአል በዚህም በአል ወንድ ሁሉ ወደቤተ መቅደሱ የመምጣት እና በእግዚአብሄር ፊት የመታየት ግዴታ አለበት (ዘጸ 34፡18-23፤ ዘዳ 16፡16)፡፡ የብሉይ ኪዳኑ የበአሉ አላማ እግዚአብሄር እስራኤልን ከግብጽ በማስቸኮል እንዳስወጣቸው ማስታወስ ሲሆን ለአዲስ ኪዳን የነበረው ትንቢታዊ ውክልና የኢየሱስ መቀበር ነው (NIV Study Bible, 1985:176-177፤ Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡ በግል ህይወት ደግሞ ከሀጢያት ልምምድ ፈጥኖ መውጣትን እና የውሃ ጥምቀትን ይወክላል (Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡

5. <u>መለከት የሚነፋበት ቀን</u>

የመለከት በአል በሰባተኛው ወር በመጀመሪያው ቀን የሚከበር እና ከማንኛውም ስራ ታቅቦ የአምልኮ ጉባኤ የሚካሄድበት በአል ነው (ዘሌ 23፡23-25)፡፡ የሚከናወኑበት የአምልኮ ተግባራት መለከት መንፋት እና መስዋእት ማቅረብ ሲሆኑ የበአሉ አላማ ጌታ ስላደረገው ቸርነት እስራኤልን በፊቱ ማቅረብ ነው (ዘሌ 23፡23-25፤ ዘሁ 29፡1፤ NIV Study Bible, 1985:176-177)፡፡ በትንቢታዊነቱ በመጨረሻው ዘመን የእስራኤልን ወደጌታ መመለስ እና በሰባተኛው መለከት ጊዜ የቤተ ክርስቲያንን ወደአንድነትና ወደጽድቅ ሙላት መምጣት የማመልከት አላማ አለው (Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡ በግል ህይወት ደግሞ የጌታን የማዳን ጥሪ ሰምቶና ተቀብሎ ወደአካሉ መቀላቀልን ያመለክታል (Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡

6. <u>የማስተስረያ ቀን</u>

የማስተስረያ ቀን አይሁድ በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን ራሳቸውን እያዋረዱ የእግዚአብሄርን ይቅርታ የሚለምኑበት በአል

ነው (ዘሌ 23፡26-32፤ የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ 1972፡106)፡፡ አላማው ህዝቡንና መቅደሱን መቀደስ ሲሆን በዚህ እለት ሁሉም ሰው ከስራ ታቅቦ በእግዚአብሄር ፊት ራሱን ያዋርዳል (ዘሌ 23፡30፤ NIV Study Bible, 1985:176-177፤ Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡ በጥላነቱ የክርስቶስን ህዝቡን የማንጻትና ለመጨረሻው ቀን ቤተ ክርስቲያንን የማዘጋጀት ተግባር ይጠቁማል (Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡ በግል ደግሞ በክርስቶስ ያለንን ቦታ ማወቅና በቅድስናና በአሸናፊነት መኳዝ እንዳለብን ያስተምረናል (Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡

## 7. <u>የመከር በዓል</u>

ይህ በአል በተለዋጭነት በአለ ሀምሳ እንዲሁም የሰባቱ ሱባኤ በአል ተብሎ ይጠራል፡፡ ከፋሲካ ከሰባት ሳምታት በኋላ የስንዴ በኩራት አጨዳን ለማሰብ የስንዴ በኩራት መስዋእት በማቅረብ እና ከማንኛውንም ስራ ታቅቦ የአምልኮ ጉባኤ በማድረግ የሚከበር በዓል ነው (ዘጸ 23፡16፤ 34፡22፤ ዘሌ 23፡21፤ ዘሁ 28፡26፤ የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ 1972፡106፤ NIV Study Bible, 1985:176-177)፡፡ እንዲሁም በሲና የህጉን መሰጠት ያሳስባል፡፡ በተለይ ለወንድ በአሉን ለማክበር ወደቤተ መቅደሱ መሄድ ግዴታ ነው፡፡ በአጠቃላይ የዳስ እና የቂጣ በአላትን ጨምሮ ወንድ ሁሉ ወደቤተ መቅደሱ ለመምጣት የሚገደድባቸውን ጊዜያት ሶስት ያደርጋቸዋል (ዘጸ 34፡18-23፤ ዘዳ 16፡16)፡፡ ለአዲስ ኪዳን ያለው ትንቢታዊ ትርጉም ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ላይ መውረዱን ማመለከቱ ሲሆን በግላችን በመንፈስ ቅዱስ እንደምንጠመቅ ይጠቁማል (Shepherd's Staff, 1993:C104-105)፡፡

## 8. <u>የሰንበት አመት</u>

የሰንበት አመት በየሰባት አመቱ አንድ ጊዜ አንድ አመት ሙሉ የሚከበር ምድርን የማሳረፍ እና ራሷን እንድታድስ እድል የመስጠት በአል ነው (ዘጸ 23፡10-11፤ ዘሌ 25፡1-7)፡፡ ማረስን፣ መዝራትን፣ ተክልን መንከባከብን እና ምርት መሰብሰብን የመሳሰሉ ስራዎች አይከናወኑም፤ ስለዚህ ከምድሪቱ ጋር አብሮ ሰውም ያርፋል፡፡ በራሱ ጊዜ የበቀለ እና ያፈራ ተክል ቢኖር ፍሬው ለመጻተኛ፣ ለእንስሳትና ለዱር አራዊት ምግብ ይሆናል፡፡ ባለመሬቱም መመገብ ይችላል፡፡ እግዚአብሄር ለአይሁድ ከዚህ የበአል አመት ቀደም ብሎ ባለው አመት የሶስት አመት ምርት እንደሚሰጣቸው እና በሰንበት አመት ምን እንበላለን የሚለው ሊያሳስባቸው እንደማይገባ ቃል ገብቶላቸዋል (ዘሌ 25፡20-22)፡፡

## 9. <u>ኢዮቤልዩ</u>

ኢዮቤልዩ በሀምሳ አመት አንድ ጊዜ አንድ አመት ሙሉ በአጠቃላይ ምድር እና ሰው ነጻነታቸውን በመቀዳጀት የሚያከብሩት በአል ነው (ዘሌ 25፡8-55፤ 27፡17-24፤ ዘሁ 36፡4)፡፡ እንደሰንበት አመት በዚህም በአል ምድር ላይ ማረስን፣ መዝራትን፣ ተክልን መንከባከብን እና ምርት መሰብሰብን የመሳሰሉ ስራዎች አይከናወኑም፤ ባሪያዎች ሁሉ ነጻ ይወጣሉ፤ እዳ ያለበትም ሰው ይሰረዝለታል፤ መሬት የሸጠ ሰው ደግሞ ከሸጠበት ዋጋ ላይ ገዢው እስከዚያ አመት ድረስ የተጠቀመው ታስቦ ቀሪውን ገንዘብ ለገዢው ይከፍልና መሬቱን መልሶ ይወስዳል፡፡ ስለዚህ በዚህ በአል በእግዚአብሄር አሰራር ማህበረሰቡ ወደነበረበት ሰብአዊ እና ኢኮኖሚያዊ ነጻነት ይመለሳል (NIV Study Bible, 1985:176-177)፡፡

## 10. <u>ፉሪም</u>

በመጽሀፈ አስቴር ውስጥ እንደተገለጸው እስራኤላውያን በምርኮ ምድር እያሉ በሀማ ትእዛዝ ፉሪም በተባለ እጣ መሰረት አዳር በተባለው ወር አስራ ሶስተኛ ቀን እንዲገደሉ የሞት አዋጅ ወጣ፡፡ ነገር ግን በመርዶክዮስ እና በአስቴር ጥረት አዋጁ ተገልብጦ አይሁድ ከሞት ተርፈው ሊገድሏቸው የተነሱትን እንዲበቀሉ ሌላ ትእዛዝ ወጣ፡፡ በትእዛዙም መሰረት አይሁድ ሊገደሉበት በነበረው አዳር አስራ ሶስት እና በሚቀጥለው ቀን ጠላቶቻቸውን ተበቀሉ፡፡ እነዚህን ከሞት ተርፈው ገዳዮቻቸውን የገደሉባቸውን እና እረፍት ያገኙባቸውን ቀናት ለማሰብ አዳር አስራ አራት እና አስራ አምስት በየአመቱ በግብዣና በስጦታ እንዲያከብሩ ታዘዘ፤ የበአሉ ቀናትም እንደእጣው ፉሪም የሚል ስም ወጣላቸው (አስ 9፡17-32)፡፡

## 11. <u>የመቅደስ መታደስ በአል</u>

ኤጲፋነስ አንጥዮኮስ የተባለው የግሪኮ-ሶሪያ ንጉስ አሳማ ሰውቶ እና ደሙን ረጭቶ ያረከሰው እዝራ ያሰራው (ሁለተኛው) መቅደስ በመቃብያን ዘመን በ165 ዓ.ዓ. እንደገና ስለተቀደሰ ያንን ለማስታወስ ይህ በአል ተደነገ (ዮሀ 10፡22፤ የመጽሀፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ 1972፡106፤ Fairchild, 2020)፡፡

## በአል በአዲስ ኪዳን

መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱት ከላይ ያየናቸው በአላት በሙሉ ለብሉይ ኪዳን ሰዎች የታዘዙ ናቸው፡፡ ለክርስቶስ ስራ ጥላዎች ወይም ሞግዚቶች ስለነበሩ እና በኢየሱስ መምጣትና የማዳን ስራ መስራት ፍጻሜያቸውን ስላገኙ በአዲስ ኪዳን አይከበሩም፤ እንዲያውም እነሱን ማክበር የክርስቶስን ስራ ከማራከስ ተለይቶ አይታይም (ገላ 4፡9-10፤ ቆላ 2፡16-19)፡፡ በተለዋጭም እንድናከብር የታዘዝነው በዓል የለም፡፡ ይህም አራት ነገሮችን ያሳየናል፡፡

አንደኛ በምድር ላይ እስካለን ድረስ በዓል የሚባል ነገር የለም፡፡ ሁሉም ተራ ቀን ነው፡፡ በዓላችን በሰማይ ወደዘላለም እረፍታችን ስንሄድ ነው፡፡ የምድር ህይወት ሌሎችን ወደወንጌሉ የምንመልስበት የስራ ጊዜ ስለሆነ በበዓል ልናባክነው አይገባም፡፡

ሁለተኛ ሁሉም ቀን በዓል ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን በበአላት ጊዜ ይደረጉ የነበሩት ንስሃ መግባቱም፣ እግዚአብሄርን ማመስገኑም፣ በጌታ ያለፍነው ታሪካችንን ማሰብም በአመት አንድ ቀን ተጠብቆ ሳይሆን ሁሉም ቀናት ላይ ይደረጋሉ፡፡ ለምሳሌ መስቀሉን እንድንሸከም የታዘዝነው በየእለቱ ነው (ሉቃ 9፡23)፡፡ እንዲሁም ኢየሱስ ሰዎች በአላት በሚሏቸው ቀናት ራሱ በቀጥታ መልካም ነገር ሰርቶ በማሳየት መልካም ስራ ሁሉ በማንኛውም ቀን እንደሚሰራ ምሳሌ ትቶልናል (ማቴ 12፡12)፡፡ ክፉ መስራት ደግሞ በማንኛውም ቀን ለማንም ክርስቲያን አልተፈቀደም፡፡ ስለዚህ ሁሉ ቀን መልካም የሚሰራበት ከሆነ ሁሉም ቀን በአል ነው ማለት ነው፡፡ በዓል ብለን የምንሰይመው የተለየ ቀን አያስፈልገንም፡፡

ሶስተኛ በአል ባስፈለገን ጊዜ እኛ ወስነን የምናደርገው ነው፤ የምንገደድበት ከእምነታችን ጋር የተያያዘ በአል የለም ማለት ነው፡፡ እግዚአብሄር በአልን ልማድ እንዳይሆንብን፣ ክርስትናን ስርአት እንዳናደርገውና ቀንን ወደማምለክ እንዳንመጣ ለመከላከል ሲል የበአል ቀንን አልወሰነም፡፡ ለምሳሌ የጌታ ራት መታሰቢያ እንድናደርግ ስንታዘዝ ቀኑ አለመወሰኑ ለዚህ ማስረጃ ነው (ሉቃ 22፡19፤ 1ቆሮ 10፡25-26)፡፡

አራተኛ በአል ማክበርም አለማክበርም የሰው ምርጫ መሆኑን ያመለክታል፡፡ እግዚአብሄር የሚያተኩረው በበአል መከበር አለመከበር ላይ ሳይሆን በማክበር አላማችን ላይ ነው (ሮሜ 14፡6)፡፡ እግዚአብሄር ለእሱ ብለን የምናከብረውን በአል ይቀበለዋል፡፡ የማያከብርም ደግሞ በበአል ሰበብ ጊዜውን እንዳያጠፋና ነጻነት እንዲያገኝ ሁሉን ቀን ነጻ ያደረገለትን ጌታ ስለሚያመሰግን በዚህም ደስ ይለዋል፡፡

በአራቱም አተረጓጎም መሰረት በአል በአዲስ ኪዳን በግልጽ ባይከለከልም የተሰጠው ቦታ አነስተኛ መሆኑን እናስተውላለን፡፡ አሁን ክርክራችን መሆን ያለበት በአል ማክበር እንችላለን ወይስ አንችልም በሚለው ላይ ሳይሆን በአል ካከበርን እንዴት እናክብር በሚለው ላይ ነው፡፡

**ይቀጥላል**

## *የቤርያ ቁጥር 37 ጥያቄዎች መልሶች (መሬት)*

1. የሴት ባሪያ እምቢቷን መውረሷ (ምሳ 30፡21-22)
2. ቆሬ፣ ዳታን፣ አቤሮንና ቤተሰባቸው፤ በአሮን ላይ በማመጻቸው (ዘሁ 16፡ 31-32)
3. መንገድ ዳር፣ ጭንጫ፣ እሾህ የበቀለበት፣ መልካም መሬት (ማቴ 13፡4-8)
4. በትር (ዘጸ 4፡3)፣ ውሀ (ዘጸ4፡9)
5. የደም መሬት ወይም አኬልዳማ (ማቴ 27፡7-8፤ ሀዋ 1፡18-19)

## *የቤርያ ጥያቄዎች (ሚስት)*

1. ጋለሞታ ሴት እንዲያገባ የታዘዘ ነቢይ ማነው?
2. እግዚአብሄር ሚስቱን በመቅሰፍት በመውሰድ ለእስራኤል ትምህርት ስለሚሰጥ ስትሞት እንዳያለቅስ የታዘዘ ነቢይ ማነው?
3. የወንድሙን ሚስት በማግባቱ የተገሰጸ ሰው ማነው?
4. ሚስቶቻቸው መንፈሳዊ ህይወታቸውን እንዲበላሽ ምክንያት ከሆኑባቸው ሰዎች መካከል አንዱን ጥቀስ፡፡
5. ሚስቶቻቸው ህይወታቸውን ከታደጉላቸው ሰዎች መካከል አንድ ጥቀስ፡፡